በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመከላከል ብቃት ያለው ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ታህሳስ 2007 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማውጫ

ክፍል አንድ 1
መግቢያ 1
የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል ራዕይና ተልዕኮ 2
የማዕከሉ ራዕይ 2
የማዕከሉ ተልዕኮ 2
የማዕከሉ ስልጣንና ተግባር 2
የማዕከሉ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል 3
ድርጅታዊ መዋቅር 3
የሰው ኃይል 4
የፋይናንስ ምንጭ 4
የኦዲቱ ዓላማ 4
ለኦዲት የተመረጠው የኦዲት አካባቢ 4
የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች 5
የትኩረት አቅጣጫ 5
የኦዲት መመዘኛ መስፈርት 5
የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ 5
የህገወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመከላከል የሚሰሩ የስራ ሥዕላዊ መግለጫ /Process Description/ 7
ክፍል ሁለት 8
የኦዲት ግኝቶች 8
2.1. ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውር ሊያስከትሉ የሚችሉ ተግባራትን ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤ 8
ኃላፊነት የተሰጣቸው መ/ቤቶች ለህገወጥ የገንዘብ ዝወወውር ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ የስጋት አካባቢዎችን መለየታቸውን በተመለከተ 8
ህገ-ወጥ የውጭ ምንዛሪ ግዥ እና ሽያጭ እንዳይፈጸም የሚደርገውን የክትትል እና ቁጥጥር ሥርዓት በተመለከተ 9
የፋይናንስ እና የፋይናንስ ነክ ያልሆኑ ተቋማት/ድርጅቶች ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመቆጣጠር የሚያስችል የውስጥ ፖሊሲና ቁጥጥር ሥርዓት ያላቸው መሆኑን በተመለከተ 10
የገቢ ወይም የወጪ ንግድ እቃዎችን ዋጋ ከተገዙበት ወይም ከተሸጡበት ትክክለኛ ዋጋ አስበልጦ ወይም አሳንሶ ማቅረብን በተመለከተ 11
በህገ ወጥ ንግድ እና የሰዎች ዝውውር ሥራ አማካኝነት የህገ ወጥ የገንዘብ ዝውውር የሚጠረጠሩትን የሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካላት ለማዕከሉ ሪፖርት ማድረጋቸውን በተመለከተ 12
ብሔራዊ ባንክ የደነገጋቸው ሁኔታዎችና ግዴታዎች ተሟልተው ዕቃዎች እንዲወጡና እንዲገቡ መደረጉን በተመለከተ፣ 14
2.2 ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመከላከል የፋይናንስ መረጃ ሥርዓት መኖሩን እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤ 16

የግል አሰሪና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ያገኙትን ገቢና በውጭ አገር ተቀጥረው የሚሰሩ ኢትዮጵያዊያን የሰሩበትን ገንዘብ ወደ ሀገር ቤት ለመላክ የሚያስችላቸው አሰራር መዘርጋቱን በተመለከተ፣ 16

2.3 ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመከላከል በባለድርሻ አካላት መካከል የተቀላጠፈ ቅንጅታዊ አሰራር ሥርዓት መኖሩን እና ተግባራዊ ደረጉን በተመለከተ፤ 18

በብሔራዊ ባንክ እና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መካከል ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር ለመከላከል የተዘረጋ ቅንጅታዊ አሰራር ስለመኖሩ፣ 18

ክፍል ሶስት 19

መደምደሚያ 19

ክፍል አራት 21

የማሻሻያ ሃሳቦች 21

አባሪ 1 24

የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል ድርጅታዊ መዋቅር 24

አባሪ 2 25

የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) 25

አባሪ 3 27

በኦዲቱ ወቅት የታዩ ባለድርሻ አካላት ዝርዝር 27

አባሪ 4 28

የዋና ዋና ባለድርሻ አካላት የሥራ ግንኙነት 28

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. ለአንድ የታዳጊ አገር ኢኮኖሚ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ በአግባቡ መጠቀምን በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ ከወጪ ንግድ እና ከተለያዩ ምንጮች የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ፣ የተለያዩ ምርቶችንና አገልግሎቶችን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሚወጣውን የውጭ ምንዛሪ አጠቃቀምን በተመለከተ ተግባራዊ የሚደረግበትን፣ የሚተዳደርበትንና ቁጥጥር የሚደረግበትን ግልጽና ቀልጣፋ የሆነ ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ የገቢ ወይም የወጪ ንግድ እቃዎችን ዋጋ ከተገዙበት ወይም ከተሸጡበት ትክክለኛ ዋጋ አስበልጦ ወይም አሳንሶ ማቅረብ (over or under invoicing of imported or exported goods) ለህገወጥ የገንዘብ ዝውውር ተግባር ምክንያት ከመሆኑም በተጨማሪ ሀገሪቷ ከገቢ እቃዎች ማግኘት ያለባትን ተገቢ ግብር እንዳታገኝ ያደርጋታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረትን ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ የፋይናንስ ሥርአቱን የተረጋጋ፣ ግልፅነት ያለው እና ቀልጣፋ እንዳይሆን ያደርጋል፡፡
2. ይህንን ለመከላከልና የወንጀል ድርጊቶቹን ለመዋጋት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ የተለያዩ ህጎችን ያጸደቀ ሲሆን፣ በዚህም መሰረት በ1997 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ህግ አንቀፅ 684፣ በተለያዩ ጊዜ በወጡት አዋጆች፣ በ2000 በአዋጅ ቁጥር 592/2000፣ በ2002 ዓ.ም አዋጅ ቁጥር 657/2002 እና በ2005 ዓ.ም አዋጅ ቁጥር 657/2002 በማሻሻል በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረትን ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር በአዋጅ ቁጥር 780/2005 ወጥቶ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡
3. በአሁኑ ጊዜ ካለው የአገር አቀፉንና የአለምን ወቅታዊ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረትን ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 657/2002 ለማስፈጸም የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል በሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 171/2002 መሰረት ተቋቁሟል፡፡

የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል ራዕይና ተልዕኮ

የማዕከሉ ራዕይ

4. "የሀገሪቱ የፋይናንስ እና የንግድ ሥርዓቱ የወንጀለኞች መጠቀሚያ ከመሆን የፀዳ፣ ጤናማ እና ተአማኒነት ያለው ሆኖ ማየት"

የሚል ነው ፡፡

የማዕከሉ ተልዕኮ

5. "በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ፣ ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመደገፍ እና ተያያዥነት ያላቸው የኢኮኖሚ ወንጀሎችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር እንዲቻል ዓለም አቀፋዊ እና ሀገራዊ ግዴታዎችና ህጎች የሚከበሩበት ማዕቀፍ /compliance frame work/ መቅረጽና ተግባራዊ ማድረግ እንዲሁም ጥራት ያለው እና ወቅታዊ የፋይናንስ መረጃ በማቅረብ የፋይናንስና የንግድ ሥርዓቱ ከእነዚህ ወንጀሎች መጠበቅ እና የሀገር ደህንነት ለማስከበር አስተዋጽኦ ማድረግ"

የሚል ነው፡፡

የማዕከሉ ስልጣንና ተግባር

6. ለማዕከሉ በአዋጅ ቁጥር 780/2005 እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 171/2002 መሰረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፡-

- በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ከማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ስጋቶች ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በአዋጁ መሰረት ይሰበስባል፣ ያከማቻል፣ ይፈትሻል፣ ይተነትናል፣ ያሰራጫል፤
- በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ከማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር በተያያዘ የሕዝቡ ግንዛቤ እንዲዳብር ያደርጋል፤
- በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ከማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን መነሻ፣ የአፈጻጸም ስልት፣ ዓይነት፣ ባህሪ እና አደጋ ያጠናል፣ ለሚመለከታቸው አካላትም የመፍትሔ አቅጣጫ ይጠቁማል፤
- የፋይናንስ ተቋማትን በመቆጣጠር ረገድ ለብሔራዊ ባንክ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ከማቅረብ እና

ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር የተያያዙ በአዋጁ የተመለከቱ ግዴታዎቻቸውን ለመወጣት የሚዷቸው የአሰራር መመሪያዎች ያወጣል፤

- በአዋጁ መሰረት ያገኛቸውን በቀላሉ ለጉዳት የሚጋለጡና ሚስጥራዊ መረጃዎችን ለመጠበቅ የሚስችል ተገቢ የመረጃ አስተዳደር ሥርዓት ያቋቁማል፤
- በአዋጁ መሰረት የተቀበላቸውን ሪፖርቶች ለህግ አስፈጻሚ አካላት የተመሩ ጉዳዩችን፣ ከተመሩት ውስጥ ምርመራ የተካሄደባቸውንና ክስ የተመሰረተባቸውን የወንጀል ጉዳዮች እና ዓለም ዓቀፍ ድጋፍ የተጠየቀባቸው ጉዳዮችን ጨምሮ ስራውን በተመለከተ የተሟላ ስታስቲክስ ይይዛል፤
- የደረሰው ሪፖርት ወይም መረጃ በማዕከሉ ግምገማ በአጁ ከተመለከቱት ወንጀሎች ውጭ ለሆነ ሌላ ወንጀል ጋር በተያያዘ ምርመራ ለማካሄድ ወይም ክስ ለመመሥረት የሚያስችል መሆኑን በበቂ ምክያት ከጠረጠረ ጉዳዩን ወዲያውኑ አግባብ ላለው ህግ አስፈጻሚ አካል ይመራል፤
- የአዋጁን ተፈጻሚነት ለማረጋገጥ በራሱ ወይም ከሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ ባለስልጣናት ጋር በመተባበር በፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ባልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች ላይ ቁጥጥር፣ ፍተሻና ክትትል ያደርጋል፤
- በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብንና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ከመከላከል ጋር በተያያዘ ሌሎች ተቋማት፣ ያቀናጃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
- ስምምነትን ወይም ሌላ ህጋዊ ሥልጣንን መሰረት በማድረግ ለሌሎች ሀገሮች አቻ ተቋማት ወይም ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች መረጃ ይሰጣል እንዲሁም ይቀበላል፤
- የአዋጁን ተፈጻሚነት ለማረጋገጥ በራሱ ወይም ከሌሎች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣናት ጋር በመተባበር ኃላፊነት ባለባቸው ሰዎች ላይ ቁጥጥርና ክትትል ያደርጋል፤
- በአዋጁ መሠረት የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን በሚጥሱ ኃላፊነት ባለባቸው ሰዎች ላይ ሊወሰድ ስለሚገባ አስተዳደራዊ እርምጃ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፤

የማዕከሉ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል

ድርጅታዊ መዋቅር

7. የፋናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ሲሆን የሚመራው በዳይሬክተሮች ቦርድ ነው፡፡ ማዕከሉ አንድ ዋና ዳይሬክተር እና አንድ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ሲኖሩት ለዋና ዳይሬክተሩ ተጠሪ የሆኑ የህግ አገልግሎት፣ የኦዲት አገልግሎት፣ የህዝብ

ግንኙነት አገልግሎት እና የሰው ኃይል ልማትና ፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ሲሆኑ እንዲሁም የፋይናንስ ግብይት ፍተሻ እና ትንተና ዳይሬክቶሬት እና የኢንፎርሜሽን ሲስተምና የፋይናንስ መረጃ ደህንነት ዳይሬክቶሬት ለም/ዋና ዳይሬክተሩ ተጠሪ እንዲሆኑ ተደርጎ ተዋቅሯል፡፡ ድርጅታዊ መዋቅሩ በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡

የሰው ኃይል

8. የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል 63 ቋሚ ሠራተኞች በመዋቅር የጸደቀለት ሲሆን እስከ ህዳር ወር 2007 ዓ.ም ድረስ 47 ቋሚ ሠራተኞች ነበሩት። ከእነዚህ ውስጥ ፕሮፌሽናል የሆኑ ወንድ 16 ሴት 15 ድምር 31 እንዲሁም ፕሮፌሽናል ያልሆኑ ወንድ 8 ሴት 8 በድምሩ 16 በጠቅላላ ወንድ 24 እና ሴት 23 በድምር 47 ሰራተኞች አሉት።

የፋይናንስ ምንጭ

9. የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል በአዋጅ እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን ከመንግስት በጀት የሚመደብለት ሲሆን ከ2004 እስከ 2006 በጀት ዓመት ድረስ የተመደበለት በጀት እና ሥራ ላይ የዋለው ወጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

በጀት ዓመት	የተፈቀደ በጀት	ስራ ላይ የዋለ በጀት	ሥራ ላይ የዋለው በጀት በመቶኛ
2004	8,591,456.00	7,150,797.00	83.23%
2005	6,147,400.00	5,336,402.00	86.81%
2006	10,380,600.00	7,147,426.28	68.85%

የኦዲቱ ዓላማ

10. የኦዲቱ አላማ ህገወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመከላከል የተዘረጋው ሥርዓት ውጤታማና ብቃት ባለው መልኩ እየተተገበረ መሆኑን እንዲሁም የተዘረጋውን ሥርዓት ለመተግበር የሚካሄደው ቅንጅታዊ አሰራር ውጤታማ መሆኑን በመገምገም የሚታዩ ችግሮችን በመለየት ችግሮቹን ለማቃለል ብሎም ለማስወገድ የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብ ነው።

ለኦዲት የተመረጠው የኦዲት አካባቢ

"ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመከላከል ብቃት ያለው ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ"

የሚል ነው፡፡

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች

የትኩረት አቅጣጫ

11. ከላይ በተገለጸው የኦዲት አካባቢን ኦዲት ለማድረግ ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ተለይተዋል፡፡ እነርሱም:-
    1. ለህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውር ምክንያት የሆኑ ተግባራትን ለመከላከል የሚያስችል ቅንጅታዊ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፤
    2. በሀገሪቱ ህገ ወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመከላከል የፋይናንስ መረጃ ሥርዓት መኖሩን እና ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፤
    3. ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመከላከል የተቀላጠፈ የባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ አሰራር ሥርዓት ሊኖር እና ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፤

የሚሉ ናቸው፡፡

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

12. ከላይ የተለዩትን ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ 26 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criterias) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህን የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለማዘጋጀት መሠረት የሆኑት የማዕከሉ የተቋቋመበት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ፤ የፋይናነስ ተቋማትን እና የፋይናንስ ነክ ያልሆኑ ተብለው የተሰየሙ የንግድ የሙያ ሥራዎች የሚመለከት ረቂቅ መመሪያዎች፣ Customer due diligence መመሪያ እና የማዕከሉ ስትራቴጂክ እቅድ እንዲሁም የመረጃ ድህረ ገጾች /web site/ ናቸው፡፡ የተዘጋጁት መመዘኛ መስፈርቶች ለማዕከሉ ተልከው አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹ በአባሪ 2 ተያይዘዋል፡፡

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

13. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ ክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመስሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው ከ2004 እስከ 2007 የመጀመሪያው ሩብ በጀት ዓመት ድረስ ያሉትን የሥራ ክንውኖችን ነው፡፡
14. ዝርዝር ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል እና ዋና ባለድርሻ አካላት የሆኑትን ብሔራዊ ባንክን ጨምሮ ሰባት የመንግስት መ/ቤቶች፣ ሁለት የመንግስት

ባንኮች እና በናሙና የተመረጡ አራት የግል ባንኮች፣ በመገኘት ለሚመለከታቸው ሠራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ ከማዕከሉ ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር ጋር ተያያዥ የሆኑ መረጃዎችን በመከለስ እና ህገወጥ የውጭ ገንዘብ ንግድ እንቅስቃሴ የሚከናወንባቸው በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ ቦታዎች በአካል በማየት ነው፡፡ በኦዲቱ ወቅት የታዩ ባለድርሻ አካላት ዝርዝር በአባሪ 3 ተያይዟል፡፡

የህገወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመከላከል የሚሰሩ የስራ ሥዕላዊ መግለጫ /Process Description/

15. ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር ምንጩ ህጋዊም ሆኑ ህጋዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚያካሂዱት ህገወጥ እንቅስቃሴ በመሆኑ እና ከገቢ እና ከወጪ እቃዎች፣ ከሌተር ኦፍ ክሬዲት አሰጣጥ ሂደት፣ ከተለያዩ የወንጀል ድርጊቶች፣ በወንጀል የተገኙ ገንዘቦችን ህጋዊ ለማስመሰል በሀገሪቱ ያሉትን የፋይናንስ እና የገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶች መጠቀምን የሚያጠቃልል በመሆኑ ዝውውሩን ለመግታት ያለው ሥርዓት እና ሂደት የተለያዩ መንግስታዊ ተቋማትን የሚያጠቃልል እና ቅንጅታዊ በሆነ አሰራር የሚካሄድ ነው፡፡ የዋና ዋና ባለድርሻ አካላት ግንኙነት በሚቀጥለው ምስል ላይ ተመልክቷል፡፡ ዝርዝር ድርሻቸው በአባሪ 4 ላይ ተያይዟል፡፡



ክፍል ሁለት

የኦዲት ግኝቶች

2.1. ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውር ሊያስከትሉ የሚችሉ ተግባራትን ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

ኃላፊነት የተሰጣቸው መ/ቤቶች ለህገወጥ የገንዘብ ዝወወውር ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ የስጋት አካባቢዎችን መለየታቸውን በተመለከተ

16. ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመከላከል ኃላፊነት የተሰጣቸው ሁሉም መ/ቤቶች ከተሰጣቸው ኃላፊነት እና ከገቢና ወጪ (import & export) ንግድ አንፃር ለህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውር ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ የስጋት አካባቢዎችን በቅድሚያ ትኩረት ሰጥተው ሊለዩ ይገባል፡፡ የፋይናንስ መረጃ ደህንነት ማዕከልም እነዚህ አካላት ግዴታቸውን አውቀው እንዲንቀሳቀሱ ለማድረግ ክትትል እና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

17. ይሁን እንጂ የህገወጥ የገንዘብ ዝውውር መከላከልን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸው የኢትዮጵያ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ብሔራዊ ባንክ፣ ንግድ ሚኒስቴር፣ ማዕድን ሚኒስቴር፣ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የፌደራል ስነምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ከተሰጣቸው ኃላፊነት አንጻር ለህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውር ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ የስጋት አካባቢዎችን ለይተው ያላስቀመጡ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ የፋይናንስ መረጃ ደህንነት ማዕከል ለህገወጥ የገንዘብ ዝውውር ምክንያት የሆኑ አካበቢዎችን በመለየት ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ማቅረባቸውን የገለጹ ሲሆን ነገር ግን ጥናቱ እንዲቀርብ ሲጠየቁ ሠነዱን በሚስጥር መያዝ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ሊቀርብ እንደማይችል ገልጸዋል፡፡

18. ስለሁኔታው ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ብሄራዊ ባንክ፣ ንግድ ሚኒስቴር፣ ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የፌዴራል ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን እና ማዕድን ሚኒስቴር ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ ኦዲቱ እስተከናወነበት ጊዜ ድረስ በህገወጥ የገንዘብ ዝውውር ዙሪያ የሰሩት የስጋት ጥናት የሌለ መሆኑን ገልፀው ወደፊት ግን ቢሰራበት ተገቢ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

19. እንዲሁም የማዕከሉ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ለህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውር ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ የስጋት አካባቢዎች በማዕከሉ ተለይተው በስትራቴጂክ ሪፖርት ተጠቃሎ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት የተላከ መሆኑን የገለጹ ሲሆን የተላከበትን ማስረጃ እንዲያቀርቡ ተጠይቀው ማስረጃው ሚስጢራዊ /confidential/ ስለሆነ ሊቀርብ እንደማይችል

መልስ ሰጥተዋል፡፡

20. የሚመለከታቸው መ/ቤቶች ከተሰጣቸው ኃላፊነት አንጻር እንደየዘርፋቸው ተጨባጭ ሁኔታ ለህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውር ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ከፍተኛ፣ መካከለኛ እና ዝቅተኛ ደረጃ ያላቸውን የስጋት አካባቢዎች ለይተው አለማስቀመጣቸው ቅድሚያ እርምጃ ሊወሰድባቸው የሚገባቸውን ስጋቶች ተለይተው ባሉት ክፍተቶች ላይ እርምጃ ለመውሰድ ካለማስቻሉም በላይ ለህገወጥ የገንዘብ ዝውውር ምክንያት የሚሆኑ ዋና ዋና ችግሮችን በመለየት ተገቢውን የፖሊሲ ማስተካከያ እና የህግ ማዕቀፍ እንዳይዘጋጅ መንስኤ ሊሆን ይችላል፡፡

ህገ-ወጥ የውጭ ምንዛሬ ግዥ እና ሽያጭ እንዳይፈጸም የሚደርገውን የክትትል እና ቁጥጥር ሥርዓት በተመለከተ

21. በአዋጅ ቁጥር 591/2000 አንጽ 10 ተ.ቁ 1 መሰረት የህገ-ወጥ የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ ግዥ እና ሽያጭ እንዳይፈጸም ብሔራዊ ባንክ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የክትትል እና ቁጥጥር የሚደረግበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ የሚዘረጋው ሥርዓትም ግብይቱን ፈጽመው በተገኙ ግለሰቦች፣ ድርጅቶች፣ ጥምረቶች ወዘተ….. ላይም ህጋዊ እርምጃ የመውሰድ እና ለማዕከሉም ቢያንስ በየወሩ ሪፖርት ማድረግን ሊያካትት ይገባል፡፡

22. ማንኛውም ሰው ከባንኮች ወይም ፈቃድ ከተሰጣቸው መንዛሪዎች ጋር ካልሆነ ወይም ከብሄራዊ ባንክ የተለየ ፍቃድ ካላገኘ በስተቀር በውጭ ምንዛሪ ግብይት ለመሰማራት እንደማይፈቀድ በብሔራዊ ባንክ አዋጅ ቁጥር 591/2000 አንጽ 10 ተ.ቁ 1 ላይ ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ ቦታዎች (በአዲስ አበባ ስታዲዮም አካባቢ፣ በብሔራዊ ባንክ ዋና መ/ቤት አካባቢ፣ በጋንዲ ሆስፒታል አካባቢ ወዘተ..) ህገወጥ የውጭ አገር ገንዘቦች ምንዛሪ ንግድ በግልፅ እንደሚካሄድ፣ በዚህ ድርጊት ላይ የሚሳተፉ ግለሰቦች የውጭ ገንዘቦችን ለመመንዘር በአካባቢው የሚያልፉ መንገደኞችን በግልጽ እንደሚጠይቁ ከብሔራዊ ባንክ ከተገኘው መረጃ እና በሥፍራው በአካል በመገኘት በማየት /Physical Observation/ ለማወቅ ተችሏል፡፡

23. ስለሁኔታው የብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሪ ክትትልና ሪዘርቭ አስተዳደር ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ ብሔራዊ ባንክ ፍቃድ ሳይኖራቸው የውጭ ምንዛሪ ጋር በተያያዘ አገልግሎት የሚሰጡ አካላትን የመቆጣጠር የስራ ድርሻ እንደሌላቸው ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የታክቲክ ወንጀል ምርመራ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ከሰጡት መልስ የውጭ ምንዛሪን የመቆጣጠር ተግባር መጀመሪያ ከብሔራዊ

ባንክ የሚጀምር በመሆኑ እና ከባንኩ ጋር ቅንጅታዊ ስራ ባለመኖሩ ኮሚሽኑ ህገወጥ የውጭ ምንዛሪ ግብይትን ብቻውን ሊቆጣጠርው የሚችለው ነገር እንዳልሆነ ገልጸዋል፡፡ የብሔራዊ ባንኩ ኃላፊ ይህን ይበሉ እንጂ የውጭ ምንዛሪ ግብይት ቁጥጥርን በበላይነት ማስተባበር ያለበት ባንኩ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

24. ስለጉዳዩ የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ይህን በተመለከተ ማዕከሉ የፍተሻ እና የትንተና ስራ በመስራት ለፌዴራል ፖሊስ ብዙ መዝገቦችን (Cases) እንዳስተላለፈ፣ መንግስት ችግሩን እንዲያውቀው ለማድረግ ከብሔራዊ ባንክ ጋር ውይይት እንደተደረገ እና ስትራቴጅክ ትንተና በማካሄድ ለሚመለከተው የመንግስት አካል እንዲያውቁት እንደተደረገ ገልጸዋል፡፡

25. ብሔራዊ ባንክ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በመሆን በአዲስ አበባና በሌሎችም ከተሞች የሚካሄደውን ህገወጥ የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ ግዢ እና ሽያጭ ላይ ቁጥጥር ባለማድረጉ የውጭ ምንዛሪ ከአገሪቱ ኢኮኖሚ እንዲሸሽ ሊያደርግ ይችላል፡፡

የፋይናንስ እና የፋይናንስ ነክ ያልሆኑ ተቋማት/ድርጅቶች ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመቆጣጠር የሚያስችል የውስጥ ፖሊሲና ቁጥጥር ሥርዓት ያላቸው መሆኑን በተመለከተ

26. የፋይናንስ እና የፋይናንስ ነክ ያልሆኑ ተቋማት /ድርጅቶች/ የደንበኞቻቸውን ማንነት /customers identification and due diligence/ ጠንቅቀው ለማወቅ የሚረዳቸው አሠራር ዘርግተው ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው፡፡ የሚዘረጉትም ሥርዓት ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመቆጣጠር የሚያችል የውስጥ ፖሊሲና ቁጥጥር ሥርዓት ሊያካትት ይገባል፡፡ ተቋማቱም ይህንን ሥርዓት ዘርግተው ተግባራዊ እንዲያደረጉ ለማስቻል ማዕከሉ ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግላቸው ይገባል፡፡

27. ባንኮች የደንበኞቻቸውን ማንነት ለመለየት ከሚረዳቸው አንዱ እና ዋነኛው የደንበኞቻቸውን ማንነት ማወቅ /customer due diligence/ ነው፡፡ ሆኖም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ የቀረበላቸው ባንኮች በሀገር ዓቀፍ ደረጃ አንድ ወጥ የሆነ ማንነትን የሚገልጽ መታወቂያ /National ID/ ባለመኖሩ ደንበኞች የባንክ ሂሳብ ለመክፈት ሲመጡ አንድ ሰው የሚሰራው ሥራ ምን እንደሆነ የማይገልፅ እና በሀገር አቀፍ ደረጃ አንድ ወጥ የሆነ ማንነትን የሚገልጽ መታወቂያ /National ID/ ባለመኖሩ ፓስፖርት እንዲሁም ከአንድ መታወቂያ በላይ የሚጠቀሙ ደንበኞችን ማንነት ሙሉ ለሙሉ እንዳያውቁ እንቅፋት እንደሆነባቸውና ሥርዓቱን ለመዘርጋት መቸገራቸውን የገለፁ ሲሆን፣ ይህ ደግሞ በህገወጥ የገንዘብ ዝውውር

ላይ ለመሰማራትና ሆን ብለው ለማሳሳት ወይም ለማጭበርበር ለሚፈልጉ ግለሰቦች መልካም አጋጣሚ ሊፈጥር እንደሚችል ገልጸዋል፡፡ ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ ተቋማትን በተመለከተ የተሰራ ስራ ስለመኖሩ በኦዲቱ ወቅት መረጃው አልቀረበም፡፡

28. ስለሁኔታው የማዕከሉ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የደንበኞች ማንነትን በትክክል ለመለየት አስቸጋሪ ቢሆንም ብሔራዊ መታወቂያ ባይኖርም ማዕከሉ የፋይናንስ ነክ ያልሆኑ ተብለው የተሰየሙ የንግድ የሙያ ሥራዎች /designated non-financial businesses and professions/ (የሪል ስቴት፣ የህግ ባለሙያዎች፣ አማካሪዎች፣ የኦዲት ድርጅቶች ወ.ዘ.ተ.) የካሽ እና ተጠርጣሪ የግብይት ሪፖርት ለማዕከሉ የሚያሳውቁበት አሰራር ለመዘርጋት በማዕከሉ በየካቲት 2006 ዓ.ም ረቂቅ መመሪያ አዘጋጅቶ እንዲጸድቅ ለሚመለከተው አካል በቅርቡ ተልኮ እንዲጸድቅ ይደረጋል በማለት ገልጸዋል፡፡

29. በማዕከሉ የተዘጋጀው ረቅቅ የፋይናንስ ነክ ያልሆኑ ተብለው የተሰየሙ የንግድ የሙያ ሥራዎች /Designated Non-Financial Businesses and Professions/ መመሪያ ለሚመለከው አካል ተልኮ እንዲጸድቅ ባለመደረጉ የካሽ እና የተጠርጣሪ የግብይት ሪፖርት ለማዕከሉ እንዲላክ ካለማስቻሉም በተጨማሪ ህገወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመከላከል በሚደረገው እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

የገቢ ወይም የወጪ ንግድ እቃዎችን ዋጋ ከተገዙበት ወይም ከተሸጡበት ትክክለኛ ዋጋ አስበልጦ ወይም አሳንሶ ማቅረብን በተመለከተ

30. የገቢ ወይም የወጪ ንግድ እቃዎችን ዋጋ ከተገዙበት ወይም ከተሸጡበት ትክክለኛ ዋጋ አስበልጦ ወይም አሳንሶ ማቅረብን (over or under invoicing of imported or exported goods) ለመከላከል ብሔራዊ ባንክ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣንና ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የክትትል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ እና ለማዕከሉ በየወሩ ሪፖርት ሊያደርግ ይገባል፡፡

31. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በተሻሻለው የብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 16 ተ.ቁ 3. ላይ የገቢ ወይም የወጪ ንግድ እቃዎችን ዋጋ ከተገዙበት ወይም ከተሸጡበት ትክክለኛ ዋጋ አስበልጦ ወይም አሳንሶ ማቅረብ (over or under invoicing of imported or exported goods) በሚሳተፉ ግለሰቦች እና ድርጅቶች ላይ ከሌሎች ቅጣቶች በተጨማሪ ድርጊቱ የተፈጸመበትን ንብረት ሶስት እጥፍ እንዲከፍሉ የተቀመጠ ቢሆንም በብሄራዊ ባንክ እና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የወጪ እና የገቢ ንግድ እቃዎችን ዋጋ ከተገዙበት ወይም ከተሸጡበት ትክክለኛ ዋጋ አስበልጦ ወይም አሳንሶ በሚያቀርቡት ላይ

በአዋጁ መሰረት እርምጃ እየተወሰደ እንዳልሆነ እንዲሁም ለፋይናንስ መረጃ ደህንነት ማዕከል ሪፖርት እንደማይደረግ ታውቋል፡፡

32. በተጨማሪም ከውጭ ሀገር ተገዝተው የሚገቡት ዕቃዎች በአብዛኛው ከተገዙበት ዋጋ አሳንሰው /under invoicing of import/ የሚያቀርቡ ሲሆን ከቀረጥ ነጻ የሚገቡ እቃዎች በአብዛኛው ከተገዙበት ዋጋ አስበልጠው /over invoicing of import/ የሚያቀርቡ መሆኑን ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ለቀረበላቸው ጥያቄ ከሰጡት መልስ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ሆኖም በአዋጁ ድንጋጌ መሰረት ለምን ተገቢውን እርምጃ እንዳልወሰዱ ምላሽ አልሰጡም፡፡
33. ስለሁኔታው የብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሪ ክትትልና ሪዘርቭ አስተዳደር ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ የወጪ ንግድ እቃዎችን ዋጋ ከተሸጡበት ትክክለኛ ዋጋ አስበልጦ ወይም አሳንሶ ማቅረብ (over or under invoicing of export) ላይ በተደጋጋሚ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ለድርጅቶቹ እንደሚፅፉ ገልጸዋል፡፡ በአዋጁ መሰረት ግን ለምን እርምጃ እንዳልተወሰደ ምላሽ አልሰጡም፡፡
34. የገቢ ወይም የወጪ ንግድ እቃዎችን ዋጋ ከተገዙበት ወይም ከተሸጡበት ትክክለኛ ዋጋ አስበልጦ ወይም አሳንሶ ማቅረብ (over or under invoicing of imported or exported goods) አነስተኛ ቀረጥና ታክስ እንዲወሰን፣ ከቀረጥ ነጻ የገቡ ዕቃዎች የእርጅና ቅናሽ (Depreciation Charge) ከፍ ለማድረግ አገሪቷ መግኘት የሚገባትን ገቢ እንዲቀንስ ከማድረጉም በተጨማሪ የጥቁር ገበያን የሚያስፋፋና ከተፈቀደላቸው የውጭ ምንዛሪ በላይ ዕቃዎችን ወደ አገር ውስጥ በማስገባት በህገ ወጥ መንገድ የተገኘ ገንዘብን ህጋዊ አስመስሎ ለማቅረብ በር ይከፍታል፡፡

በህገ ወጥ ንግድ እና የሰዎች ዝውውር ሥራ አማካኝነት የህገ ወጥ የገንዘብ ዝውውር የሚጠረጠሩትን የሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካላት ለማዕከሉ ሪፖርት ማድረጋቸውን በተመለከተ

35. የንግድ ሚኒስቴር፣ ማዕድን ሚኒስቴር እና ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በህገ ወጥ ንግድ እና ህገ ወጥ የማዕድን ማውጣት ሥራ እንዲሁም በውጭ አገር ሥራ በማስቀጠር አማካኝነት የሚገኝ የውጭ ምንዛሪን ሆነ ብር በሕገወጥ መልክ ያዘዋውራሉ ብለው የሚጠረጥሩትን ማንኛውም ግለሰብም ሆነ ድርጅት ለማዕከሉ በየወሩ ሪፖርት የሚያቀርቡበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደረጉ ይገባል፡፡
    - ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች፡- የንግድ

ሚኒስቴር፣ የማዕድን ሚኒስቴር እና የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር መከላከልን በተመለከተ ከፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ባለመኖሩ ንግድ ሚኒስቴር በህገ ወጥ ንግድ ስራ፣ ማዕድን ሚኒስቴር ህገ ወጥ የማዕድን ማውጣት ስራ እና ሰራተኛና ማህበራዊ ሚኒስቴር በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በህገወጥ መንገድ በግለሰቦች ወይም በኤጀንሲዎች በኩል የሚደረግ ህገወጥ የውጭ አገር ገንዘብ ዝውውር ሲያጋጥማቸው ለማዕከሉ ሪፖርት የማያደርጉ መሆኑን፣

- ለኢትዮጵያውያን ዜጎች ብቻ በተከለለ የንግድ ዘርፍ ውስጥ ተሰማርተው እየሰሩ የሚገኙ 84 የውጭ ባለሀብቶች እንዲሁም በኢንቨስትመንት ፈቃድ ያልታቀፉ ወይም እንደዜጋ ተቆጥረው የዜግነት ፈቃድ አግኝተው ሥራ እንዲሰሩ ሳይፈቀድላቸው እንደሀገር ውስጥ ባለሀብት ተቆጥረው ከአስራ አምስት ዓመት በላይ በኢትዮጵያ የቆዩና በተለያየ የንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ 162 ድርጅቶች በድምሩ 246 የውጭ ሀገር ድርጅቶችና ግለሰቦች መኖራቸው በሀገር ውስጥ ያፈሩትን ገንዘብ በህገወጥ መንገድ ከሀገር ሊያሸሹ እንደሚችሉ ከንግድ ሚኒስቴር ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ እና በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ መቻሉን ነገር ግን ጉዳዩ ለማዕከሉ ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ፣
- በሀገሪቱ ውስጥ የሚመረቱት የማዕድን ምርቶች በሚመረቱበት ወቅት ምን ያህል እንደተመረተ እና ምን ያህሉ ለገበያ እንደቀረበ የሚያሳይ ሪፖርት ለማዕድን ሚኒስቴር እንዲቀርብ የማይደረግ እና በማዕድን ሚኒስቴርም የተዘረጋ የቁጥጥር ሥርዓት አለመኖሩ፣ በሀገር ውስጥ የሚመረቱ የከበሩ ማዕድናት የጥራት ደረጃ መለኪያ ባለመኖሩ ደረጃ የሚወጣለት ናሙናውን ወደ ውጭ ሀገር በመላክ ስለሆነ፣ የናሙና ማዕድኑን ውጭ ሀገር ይዞ የሚሄደው ማዕድኑን ያወጣው ድርጅት ስለሆነ ደረጃውን አሳንሶ ሊያስራ እንደሚችል ስጋት መኖሩን፣
- በቦሌ አለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ የከበሩ ማዕድናት ቁጥጥር ስራ ላይ የተሰማሩት ባለሙያዎች ስለማዕድናት በቂ ዕውቀት የሌላቸው ከመሆኑም በላይ በቀላሉ መለየት የሚችል መሳሪያም የሌለ በመሆኑ እና በኮንትሮባንድ መልክ ወደ ውጭ ሀገር ሲወጡ ሀገሪቱ ከማዕድን ምርት ሽያጭ ማግኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሪ እንድታጣ የሚደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ በሀገር ውስጥ ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር እንዲስፋፋ የሚያደርግ መሆኑን፣

ለማወቅ ተችሏል፡፡

36. የንግድ ሚኒስቴር፣ የማዕድን ሚኒስቴር እና የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር መከላከልን በተመለከተ ከፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ባለመኖሩ በንግድ ሚኒስቴር በህገ ወጥ ንግድ ስራ የተሰማሩ እንዲሁም ለኢትዮጵያውያን ብቻ የተከለለን ስራ የሚሰሩ 246 የውጭ ሀገር ዜጎች መኖራቸው፣ በማዕድን ሚኒስቴር በሀገሪቱ በሚወጡ እና ወደ ውጭ ሀገር በሚላኩት ማዕድናት ላይ የሚደረገው ቁጥጥር የላላ መሆኑ እና በሰራተኛና ማህበራዊ ሚኒስቴር በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሰርተው ያገኙትን የውጭ ምንዛሪ በህገወጥ መንገድ በግለሰቦች እንደሚልኩ ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ለታክቲክ ወንጀል ምርመራ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ከሰጡት መልስ ለመረዳት ተችሏል፡፡

37. በጉዳዩ ዙሪያ የንግድ ሚኒስቴር፣ የማዕድን ሚኒስቴር እና የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኔስቴር ለቀረበ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ በህገወጥ ንግድ ዙሪያ እንደተሳተፉ የሚጠረጥሯቸውንም ሆነ ሲሳተፉ ያገኟቸውን ግለሰቦች/ድርጅቶች ለፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል እንደማይልኩ ገልፀዋል፡፡

38. ስለጉዳዩ ማዕከሉ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከሁሉም መ/ቤቶች መረጃ ለማግኘት ያጋጠመን ችግር ባይኖርም መ/ቤቶቹ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብንና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ጋር የተያያዘ የሚመስል የሚጠረጥሩት ጉዳይ ሲያጋጥማቸው ለማዕከሉ መላክ እንዳልጀመሩ ገልጸው ቢሆንም ግን የተገለጹት ችግሮች መኖራቸውን ከሚደርሰው ጥቆማ እና ከባንኮች ተጠርጣሪ የግብይት ሪፖርት መረዳት መቻሉን ገልጸዋል፡፡.

39. ቅንጅታዊ አሰራር ባለመኖሩ እየተፈጸሙ ያሉት ግድፈቶች ሀገሪቱ ማግኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሪ ከማሳጣቱም ባሻገር፣ የሀገሪቱ ሀብት ወደ ውጭ ሀገር እንዲያሸሹ እና ባልተፈቀደላቸው የሥራ መስክ ተሰማርተው በሕገወጥ መንገድ ያገኙትን ሀብት ህጋዊ አድርገው እንዲያቀርቡ በር ይከፍታል፡፡

ብሔራዊ ባንክ የደነገጋቸው ሁኔታዎችና ግዴታዎች ተሟልተው ዕቃዎች እንዲወጡና እንዲገቡ መደረጉን በተመለከተ፣

40. የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን ብሔራዊ ባንክ የደነገጋቸው ሁኔታዎችና ግዴታዎች መሟላታቸውን እያረጋገጠ ማናቸውም ዋጋ ያላቸው ዕቃዎች ወይም የውጭ ምንዛሬ ከኢትዮጵያ እንዲወጡም ሆነ እንዲገቡ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ

ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

41. ይሁን እንጂ አንድ ሰው ከኢትዮጵያ ይዞ ሊወጣ የሚችለው የኢትዮጵያ የገንዘብ ኖት መጠን ብር 200 ብቻ እንደሆነ በብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 591/2008 አንቀጽ 16 ተ.ቁ 4. ቢሆንም ወደ ጅቡቲ ለሚሄዱ የከባድ መኪና ሹፌሮች ከብር 15,000 እስከ 30,000 ድረስ ይዘው እንደሚወጡ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

42. ስለጉዳዩ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የድንበር አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ ጅቡቲ እና ኢትዮጵያ ባላቸው የጋራ ስምምነት መሰረት ጅቡቲ ውስጥ የኢትዮጵያ ብር ኖት ተቀባይነት ስላለው ወደ ጅቡቲ እቃ ጭነው የሚሄዱ ሹፌሮች ለሚቆዩባቸው ሶስት እና ከዛ በላይ ቀናት ብር 200 ብቻ ይዘው እንዲሄዱ ቢደረግ ገንዘቡ በቂ ባለመሆኑ ባለስልጣኑ እስከ ብር 30,000 ድረስ ይዘው እንዲወጡ እንደሚፈቅድላቸው እና የብር 200 የገንዘብ ጣሪያ እንዲስተካከል ብሔራዊ ባንክን በተደጋጋሚ በስብሰባዎች እና በስልክ በተደጋጋሚ ቢጠይቁም እስከአሁን ምላሽ እንዳላገኙ እና በደብዳቤ እንዳልጠየቁ ገልጸዋል፡፡ የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል ም/ዋና ዳይሬክተር ተጠይቀው ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ተጠርጣሪ የግብይት ሪፖርት መላክ ስላልተጀመረ ችግሩ መኖሩን ገልጸዋል፡፡

43. በብሔራዊ ባንክ ድንጋጌ መሰረት አንድ ሰው ከኢትዮጵያ ይዞ ሊወጣ የሚችለው የኢትዮጵያ የገንዘብ ኖት መጠን ብር 200 ብቻ መሆኑ እየታወቀ ብሔራዊ ባንክ በጥናት ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ባላሳለፈበት ሁኔታ ወደ ጅቡቲ ለሚሄዱ የከባድ መኪና ሹፌሮች ከብር 15,000 እስከ 30,000 ድረስ ይዘው እንዲወጡ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መፈቀዱ ህገወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመከላከል በሚደረገው እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

2.2 ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመከላከል የፋይናንስ መረጃ ሥርዓት መኖሩን እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

የግል አሰሪና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ያገኙትን ገቢና በውጭ አገር ተቀጥረው የሚሰሩ ኢትዮጵያዊያን የሰሩበትን ገንዘብ ወደ ሀገር ቤት ለመላክ የሚያስችላቸው አሰራር መዘርጋቱን በተመለከተ፣

44. ወደ ውጭ አገር ሠራተኞችን የሚልኩ አገናኝ ኤጀንሲዎች በሚልኩበት አገር ያለው አገናኝ ኤጀንሲ በውጭ ምንዛሪ የሚከፈላቸው ገንዘብ ግልጽነት ባለው መልክ ወደ አገር ውስጥ ባለ ባንክ መግባቱ የሚረጋገጥበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በውጭ አገር የሚኖሩ እና በሀገር ውስጥ ያሉ አስቀጣሪ ኤጀንሲዎች የሰሩበትን ገንዘብ ወደ ሀገር ቤት ለመላክ የሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያ ኤምባሲም ሆነ በሌላ መንገድ ገንዘባቸውን የሚልኩበት ህጋዊ አሰራር ሊመቻችላቸው ይገባል፡፡

45. በኦዲቱ ወቅት የግል አሰሪና ሠራተኛ ኤጀንሲዎች ወደ ውጭ አገር በህጋዊ መንገድ ሠራተኞችን ለመላክ ያገኙትን የውጭ ምንዛሪ መጠን ወጥ በሆነ መልክ ባይሆንም ለሠራተኛና ማህበራዊ ሚኒስቴር የሚያሳውቁ መሆኑን ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከኢትዮጵያ በህገወጥ መንገድ ወደ ተለያዩ አረብ ሀገራት የሄዱ ዜጎች የሰሩበትን ገንዘብ ወደ ሀገር ቤት ለመላክ የሚያስችላቸው ተደራሽ የሆነ ህጋዊ የመላኪያ መንገድ እንዲኖራቸው የሚያስችል በአቅራቢያቸው በሚገኘው የኢትዮጵያ በኤምባሲም ሆነ ቆንጽላ ጽ/ቤት በኩል እንዲሁም በብሔራዊ ባንክ በኩል የተዘረጋ ስርዓት ባለመኖሩ ዜጎች ለዘመዶቻቸው በህገወጥ መንገድ በግለሰቦች እና በኤጀንሲዎች በኩል የሚልኩ መሆኑንና ይህም ለጥቁር ገበያ መስፋፋት ምክንያት መሆኑን በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የታክቲክ ወንጀል ምርመራ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ከሰጡት መልስ ለመረዳት ተችሏል፡፡

46. ስለጉዳዩ የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ይህ ችግር በሀገራችን ላይ እያስከተለ ያለው ጉዳት በተመለከተ ከብሔራዊ ባንክ ጋር ውይይት እንደተደረገ እና ስትራቴጂካዊ ትንተና በማካሄድ ለሚመለከተው የመንግስት አካል ሪፖርት እንደተደረገ እንዲሁም በዚህ ህገወጥ ስራ ላይ የተሰማሩት በጣም ብዙ ስለሆኑ በመቅጣት ብቻ የሚፈታ እንዳልሆነና ከውጭ ገንዘብ የሚልኩ ሰዎች ህጋዊ መንገድ እንዲከተሉ ለማድረግ የሚያስችል አሰራር ስርዓት በሚመለከታቸው አካላት መዘርጋት ተገቢ እንደሚሆን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ /Fact Sheet/ ላይ በሰጡት አስተያየት በህጋዊ መንገድ የሄዱትም ጭምር በህገ-ወጥ መንገድ የሚልኩ መሆናቸውን እንደሚያውቁ ገልጸዋል፡፡

47. በውጭ አገር በተለይም አረብ ሀገራት የሚኖሩት ኢትዮጵያዊያን ሰርተው ያገኙትን የውጭ ገንዘብ ወደ ሀገር ቤት በቀላሉ ለመላክ የሚያስችላቸው ተደራሽ የሆነ ህጋዊ የመላኪያ መንገድ እንዲኖራቸው የሚያስችል በኤምባሲም ሆነ በብሔራዊ ባንክ በኩል የተዘረጋ ስርዓት ባለመኖሩ ዜጎች ለዘመዶቻቸው በህገወጥ መንገድ በግለሰቦች እና በኤጀንሲዎች በኩል እንደሚልኩ ታውቋል፡፡ ይህ አሰራር ሀገሪቱ ማግኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሪ እንዳታገኝ ከማድረጉም በተጨማሪ በህገወጥ መንገድ በግለሰቦች እጅ የሚገባው የውጭ ምንዛሪ በአዲስ አበባ እየተሰፋፋ ያለውን የውጭ ምንዛሪ ጥቁር ገበያ ንግድ እንዲስፋፋ የራሱን አስተዋጽዖ አድርጓል፡፡

2.3 ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመከላከል በባለድርሻ አካላት መካከል የተቀላጠፈ ቅንጅታዊ አሰራር ሥርዓት መኖሩን እና ተግባራዊ ደረጉን በተመለከተ፤

በብሔራዊ ባንክ እና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መካከል ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር ለመከላከል የተዘረጋ ቅንጅታዊ አሰራር ስለመኖሩ፣

48. ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ እና ከሀገር የሚወጡ የውጭ ምንዛሬ ሊያስገኙ የሚችሉ ማንኛውም ግብይቶችን በሚመለከት ብሔራዊ ባንክ እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በጋራ ለመስራት የሚያስችል የተቀናጀ ሥርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

49. ብሔራዊ ባንክ ለገቢ እና ለወጪ ዕቃዎች ፈቃድ ሲሰጥ (import and export permission) ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጋር በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለመታገዙ በመ/ቤቶቹ መካከል የሚደረጉትን የመረጃ ልውውጦች ወይም መፃፃፎችን ይዘው የሚሄዱት እራሳቸው ባለጉዳዩች /አስመጪ እና ላኪ ነጋዴዎች/ እንደሆኑ፣ በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት ከሀገር መውጫ ድንበር አካባቢ በጋላፊ እና በቦሌ አለምአቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ የመንገደኞች ጓዝ ውስጥ ህገወጥ የገንዘብ እንቅስቃሴን ለመፈተሽ፣ ለመያዝ እና የተገኘውን የህገወጥ ገንዘብ መጠን ሪፖርት ለማድረግ የተዘረጋ ሥርዓት ባለመኖሩ በተመደቡት ሠራተኞች ታማኝነት ላይ ብቻ የተመሰረተ ሥርዓት በመሆኑ የቁጥጥር ስራው የላላ እንዲሆን ማድረጉን ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የድንበር አስተዳደርና ኮንትሮባንድ ክትትል ዳይሬክተር በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልጸዋል፡፡

50. ስለጉዳዩ የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ይህ ስራ ለመከላከል ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በጋራ መሰራት የሚገባ ሆኖም ግን ድንበር ተሻጋሪ ግብይቶችን በተመለከተ ለማዕከሉ ሪፖርት ማድረግ ግን በአዋጁ በግልጽ ያልተቀመጠ ቢሆንም ማዕከሉ ለስራ የሚያስፈልገውን ማንኛውንም ዓይነት መረጃ የመጠየቅ ኃላፊነት ስላለበት ከባለስልጣን መ/ቤቱ ሪፖርቶቹን ለማግኘት የሚያስችለውን መመሪያ እየተዘጋጀ ስለሆነ መመሪያው ሲጸድቅ ሪፖርት የመቀበል ስራ እንደሚጀምር ገልጸዋል፡፡

51. በብሔራዊ ባንክ እና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መካከል የመረጃ ልውውጥ ሥርዓቱ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለመታገዙ ለገቢ እና ለወጪ ዕቃዎች ፈቃድ ሲሰጥ (import and export permission) የመረጃ ልውውጡ በሐርድ ኮፒ /Hard Copy/ ስለሚከናወን መረጃዎቹን ይዘው የሚቀሳቀሱት ባለጉዳዩቹ ራሳቸው በመሆናቸው ለህገወጥ /ፎርጅድ/ ማስረጃዎች መንገድ በመክፈት ለህገወጥ ገንዘብ ዝውውር የሚያጋልጥ በር ሊከፍት ይችላል፡፡

ክፍል ሶስት

መደምደሚያ

52. ህገወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመከላከል የተዘረጋው ሥርዓት ውጤታማና ብቃት ባለው መልኩ እየተተገበረ መሆኑን እንዲሁም የተዘረጋውን ሥርዓት ለመተግበር የሚካሄደው ቅንጅታዊ አሰራር ውጤታማ መሆኑን ሲገመገም የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ተገኝተዋል፡-

- ❖ የኢትዮጵያ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ብሔራዊ ባንክ፣ ንግድ ሚኒስቴር፣ ማዕድን ሚኒስቴር፣ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የፌደራል ስነምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ከተሰጣቸው ኃላፊነት አንጻር ለህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውር ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ የስጋት አካባቢዎችን ለይተው ያላስቀመጡ መሆኑ፣
- ❖ በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ ቦታዎች ህገወጥ የውጭ አገር ገንዘቦች ምንዛሪ ንግድ በግልፅ እንደሚካሄድና ለመቆጣጠር ቅንጅታዊ አሰራር የሌለ መሆኑ፣
- ❖ የፋይናንስና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ ተቋማት የደንበኞቻቸውን ማንነት በትክክል ለመለየት በሀገር አቀፍ ደረጃ አንድ ወጥ የሆነ ማንነትን የሚገልጽ መታወቂያ /National ID/ አለመኖሩ ከአንድ መታወቂያ በላይ የሚጠቀሙ ደንበኞችን ካሉ የእነርሱን ማንነት ሙሉ ለሙሉ ማወቅ አስቸጋሪ ማድረጉ፣
- ❖ በብሔራዊ ባንክ እና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የወጪ እና የገቢ ንግድ እቃዎችን ዋጋ ከተገዙበት ወይም ከተሸጡበት ትክክለኛ ዋጋ አስበልጦ ወይም አሳንሶ ማቅረብን ለመከላከልም ሆነ ለመቆጣጠር የተዘረጋ ስርዓት ተግባራዊ አለመሆኑ፣ ከውጭ ሀገር ተገዝተው የሚገቡት ዕቃዎች ከተገዙበት ዋጋ አሳንሰው /under invoicing of import/ ከቀረጥ ነጻ የሚገቡ እቃዎች ዋጋ አስበልጠው /over invoicing of import/ የሚያቀርቡት ላይ መወሰድ የነበረበትና ቅጣት የማይወሰድ እንዲሁም፣ ለፋይናንስ መረጃ ደህንነት ማዕከል ሪፖርት የማይደረግ መሆኑ፤
- ❖ በህገ ወጥ ንግድ ስራ፣ ህገ ወጥ የማዕድን ማውጣት ስራ እና በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በህገወጥ መንገድ በግለሰቦች ወይም በኤጀንሲዎች በኩል የሚደረግ ህገወጥ የውጭ አገር ገንዘብ ዝውውር ሲያጋጥማቸው ሥልጣንና ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት ለፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል የማያሳውቁ/ ሪፖርት የማያደርጉ መሆኑ፣
- ❖ ለኢትዮጵያውያን ዜጎች ብቻ በተከለለ የንግድ ዘርፍ ውስጥ ተሰማርተው እየሰሩ የሚገኙ 84 የውጭ ባለሀብቶች እንዲሁም በኢንቨስትመንት ፈቃድ ያልታቀፉ ወይም እንደዜጋ ተቆጥረው የዜግነት ፈቃድ አግኝተው ሥራ እንዲሰሩ ሳይፈቀድላቸው እንደ ሀገር ውስጥ ባለሀብት ተቆጥረው ከአስራ አምስት ዓመት በላይ በኢትዮጵያ የቆዩና በተለያየ የንግድ ስራ

ላይ የተሰማሩ 162 ድርጅቶች በድምሩ 246 የውጭ ሀገር ድርጅቶችና ግለሰቦች መገኘታቸው የሀገሪቱ ሀብት ወደ ውጭ እንዲሸሽ /Capital flight/ የሚያደርግ መሆኑ፣

- ❖ በሀገሪቱ ውስጥ የሚመረቱት የማዕድን ምርቶች በሚመረቱበት ወቅት ምን ያህል እንደተመረተ እና ምን ያህሉ ለገበያ እንደቀረበ ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት በማዕድን ሚኒስቴር የተዘረጋ የቁጥጥር ሥርዓት አለመኖሩ፣
- ❖ በሀገር ውስጥ የጥራት ደረጃ መለኪያ ባለመኖሩ ደረጃ የሚወጣለት ናሙናውን ወደ ውጭ ሀገር በመላክ ስለሆነ፣ የናሙና ማዕድኑን ውጭ ሀገር ይዞ የሚሄደው ማዕድኑን ያወጣው ድርጅት ስለሆነ ደረጃውን አሳንሶ ለማሰራትና ዋጋን አሳንሶ ለማቅረብ ክፍተት የፈጠረ መሆኑ፣
- ❖ በቦሌ አለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ የከበሩ ማዕድናት ቁጥጥር ስራ ላይ የተሰማሩት ባለሙያዎች ስለማዕድናት ባህሪያት ዕውቀት የሌላቸው እና በቀላሉ ለመለየት ሊረዳቸው የሚችል የፍተሻ መሳሪያም የሌላቸው መሆኑ፣
- ❖ አንድ ሰው ከኢትዮጵያ ይዞ ሊወጣ የሚችለው የኢትዮጵያ የገንዘብ ኖት መጠን ብር 200 ብቻ ቢሆንም ወደ ጅቡቲ ለሚሄዱ የከባድ መኪና ሹፌሮች ከብር 15,000 እስከ 30,000 ድረስ ይዘው እንዲወጡ የሚደረግ መሆኑና በብሔራዊ ባንክ በኩል ህጉ ያልተሻሻለ ወይንም ድርጊቱ ላይ ክልከላ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ❖ ወደ ተለያዩ አረብ ሀገራት የሄዱ የሀገሪቱ ዜጎች የሰሩበትን ገንዘብ ወደ ሀገር ቤት በህጋዊ መንገድ ለመላክ የሚያስችላቸው በኢትዮጵያ ኤምባሲ፣ ቆንስላ ጽ/ቤቶችም ሆነ በብሔራዊ ባንክ በኩል የተዘረጋ ስርዓት ባለመኖሩ ዜጎች ለዘመዶቻቸው በህገወጥ መንገድ በግለሰቦች እና በኤጀንሲዎች በኩል የሚልኩ መሆኑ፤
- ❖ ብሔራዊ ባንክ ለገቢ እና ለወጪ ዕቃዎች ፈቃድ ሲሰጥ (import and export permission) ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጋር በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለመታገዙ በመ/ቤቶቹ መካከል የሚደረጉትን የመረጃ ልውውጦች ወይም መፃፃፎችን ይዘው የሚሄዱት ባለጉዳዮች /አስመጪ እና ላኪ ነጋዴዎች/ መሆናቸው ህለገወጥ (ፎርጅድ) ማስረጃዎችን ለማዘጋጀት በር የሚከፍት መሆኑና በተሳሳተ ማስረጃ እቃቸውን እንዲያሳልፉ መንገድ ሊከፍት መቻሉ፤

ታውቋል።

53. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሃሳቦች

የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅት በመፍጠር ህገወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመከላከል የሚያስችል ብቃት ያለው ሥርዓት በመዘርጋትና ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡-

- የኢትዮጵያ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ብሔራዊ ባንክ፣ ንግድ ሚኒስቴር፣ ማዕድን ሚኒስቴር፣ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የፌደራል ስነምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን የተቋቋሙበት ዓላማና ከተሰጣቸው ኃላፊነት አንጻር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሥራቸው ከገንዘብ ዝውውር ጋር የተያያዘ በመሆኑ በየዘርፋቸው ለህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውር ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ የስጋት አካባቢዎችን ሊለዩ፣ በየጊዜው ወቅታዊ ሊያደርጉ የሚያስችል አሠራር ዘርግተው ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ የፋይናንስ መረጃ ደህንነት ማዕከልም በየጊዜው የሚከሰቱ የተለያዩ ለውጦችን በማካካት በእነዚህ ተቋማት ሊለዩና መከላከያ ሊበጅላቸው በሚገባቸው አካባቢዎች ላይ ድጋፍ ሊያድርግና አፈጻጸማቸውንም ሊከታተል ይገባል፡፡
- በአዲስ አበባ ከተማም ሆነ በሌሎች የአገሪቱ ከተሞች በተለያዩ ቦታዎች በግልፅ የሚካሄደውን ህገወጥ የውጭ አገር ገንዘቦች ምንዛሪ ንግድ ለማስቆምና የምንዛሪ አገልግሎት በባንክና እንደባንክ የመመንዘር አገልግሎት እንዲሰጡ ፈቃድ በተሰጣቸው አካላት ብቻ እንዲከናወን ጉዳዩ በዋነኛነት የሚመለከታቸው የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል፣ ብሔራዊ ባንክ፣ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን እና ሌሎች የመንግስት አካላት በተቀናጀ መልክ ተከታታይ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርጉ፣ ህብረተሰቡም የህገወጥ ምንዛሪ አገልግሎት በአገሪቱ ኢኮኖሚም ሆነ ደህንነት ላይ የሚያመጣውን ሥጋት እንዲገነዘብ ለማድረግ የሚረዳ የግንዛቤ እንዲያገኙ የሚያደርጉበትን አሠራር ዘርግተው ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡
- የፋይናንስ ተቋማት የደንበኞቻቸውን ማንነት ለማወቅ /customer due diligence/ በሀገር ዓቀፍ ደረጃ አንድ ወጥ የሆነ ማንነትን የሚገልጽ መታወቂያ /National ID/ መኖሩ ከፍተኛ ጠቀሜታ ስላለው የዚህ ተግባራዊነት እንዲፋጠን የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌዴራልም ሆነ የክልል የመንግስት አካላት ጋር በመነጋገር ተግባራዊ እንዲደረግ የራሱን ግፊት ሊያደርግ ይገባል፡፡ የፋይናንስ ነክ ያልሆኑ ተብለው የተሰየሙ የንግድ የሙያ ሥራዎች /designated non-financial businesses

and professions/ (የሪል ስቴት፣ የህግ ባለሙያዎች፣ አማካሪዎች፣ የኦዲት ድርጅቶች ወ.ዘ.ተ.) የካሽ እና ተጠርጣሪ የግብይት ሪፖርት ለማዕከሉ የሚያሳውቁበት አሰራር ለመዘርጋት በማዕከሉ በየካቲት 2006 ዓ.ም የተዘጋጀው ረቂቅ መመሪያ ጸድቆ ተግባራዊ እንዲደረግ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ❖ በብሄራዊ ባንክ እና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የወጪ እና የገቢ ንግድ እቃዎችን ዋጋ ከተገዙበት ወይም ከተሸጡበት ትክክለኛ ዋጋ አስበልጦ ወይም አሳንሶ /under and over invoicing of import and export/ የቀረጥ ነጻ መብት ተጠቃሚ የሆኑትን ጨምሮ በሚያቀርቡት ላይ በተቀመጠው ህግ በሚያዘው መሰረት ተገቢ እርምጃ ሊወሰድ እና በእንደዚህ አይነት ተግባራት ላይ ተሰማርተው ሀብት ወይንም ገንዘብ እንዳገኙ የሚጠረጥሯቸውን ግለሰቦች ወይም ድርጅቶችን መረጃዎች በየጊዜው ለማዕከሉ የሚተላለፍበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ❖ በህገ ወጥ ንግድ ስራ፣ ህገ ወጥ የማዕድን ማውጣት ስራ እና በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በህገወጥ መንገድ በግለሰቦች ወይም በኤጀንሲዎች በኩል የሚደረግ ህገወጥ የውጭ አገር ገንዘብ ዝውውር ልውውጥ ጋር የተያያዙ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል የዘርፍ መ/ቤቶች የማስተካከያ እርምጃ ሊወስዱ እና በእንደዚህ አይነት ተግባራት ላይ ተሰማርተው ሀብት ወይንም ገንዘብ እንዳገኙ የሚጠረጥሯቸውን ግለሰቦች ወይም ድርጅቶችን ደግሞ ለማእከሉ ሪፖርት የሚያሳወቁበት የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡
- ❖ ለኢትዮጵያውያን ዜጎች ብቻ በተከለለ የንግድ ዘርፍ ውስጥ የውጭ ዜጎች ተሰማርተው እንዳይሰሩ ጉዳዩ የሚመለታቸው የፌዴራልና የክልል አስፈጻሚ አካላት በመቀናጀት ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ በህገወጥ መንገድ ካፒታል ወደ ውጭ ሀገር እንዳያሸሹ ሊያደርግ የሚያስችል ሥርዓት ሊዘረጋ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ❖ ማዕድን ሚኒስቴር በሀገሪቱ ውስጥ የሚመረቱት የማዕድን ምርቶች አምራቾች ምን ያህል እንዳመረቱ እና ምን ያህል ለገበያ እንዳቀረቡ በየወቅቱ ሪፖርት እንዲቀርብለት ፣ እንዲሁም ውጭ ሀገር ተልከው ደረጃ ለሚወጣላቸው የማዕድን ምርቶች ደረጃቸውን በማሳነስ እንዳይቀርብ ትክክለኛ በአገሪቱ የሚመረቱ ማዕድናት ደረጃ የሚታወቅበት ሥርዓት ሊዘረጋና ሊተገበር እንዲሁም በእንደዚህ አይነት ተግባራት ላይ ተሰማርተው ሀብት ወይንም ገንዘብ እንዳገኙ የሚጠረጥሯቸውን ግለሰቦች ወይም ድርጅቶችን ለማዕከሉ ሊያሳውቁ የሚያስችል የቁጥጥር እና የክትትል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- በአገሪቱ የመውጫ በሮች ላይ የህገወጥ ዕቃዎች ዝውውር ቁጥጥር ላይ የተመደቡ ሠራተኞች የከበሩ ማዕድናት በህገወጥ መንገድ ከአገር እንዳይወጡ የተጠናከረ ቁጥጥር ማድረግ እንዲችሉ ለባለሙያዎች ስለማዕድናት ባህሪያት የግንዛቤ ስልጠና ሊሰጣቸውና የተጠናቀረ የፍተሻ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ እንዲህ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥምም ማዕከሉ ሪፖርት ሊደረግለት ይገባል፡፡
- በብሔራዊ ባንክ ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በላይ ወደ ጅቡቲ ለሚሄዱ የከባድ መኪና ሹፌሮች መመሪያው ተጠብቆ የሚሰራበት ሁኔታ እየተፈቀደ ያለው የገንዘብ መጠን ወይ መመሪያው በፍጥነት የሚስተካከልበት ሁኔታ እንዲመቻች የሚመለከታቸው አካላት በመቀናጀት መፍትሔ ሊሰጡት ይገባል፡፡
- የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች፣ ቆንስላ ጽ/ቤቶች እና ብሔራዊ ባንክ በጋራ ውጭ ሀገራት የሚኖሩት ኢትዮጵያውያን የሰሩበትን ገንዘብ ወደ ሀገር ቤት ለመላክ የሚያስችላቸው ተደራሽ የሆነ ህጋዊ የመላኪያ መንገድ እንዲኖራቸው የሚያስችል ስርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡
- ብሔራዊ ባንክ ለገቢ እና ለወጪ ዕቃዎች ፈቃድ ሲሰጥ (import and export permission) የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ወደ አገር ውስጥ የሚገባው ወይም የሚወጣው በተሰጠው ፈቃድ መጠን መሆኑን ሊያረጋግጥና ከዚህ ጋር የተያያዙ መረጃዎችንም ባንኩና ባለስልጣኑ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የታገዘ የጋራ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

54. በመጨረሻም የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል፣ በኦዲት ወቅት የታዩት ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ ባለስልጣን መ/ቤቶች እና በናሙና የተመረጡ የፋይናንስ ተቋማት የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች በኦዲቱ ወቅት ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

አባሪ 1

የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል ድርጅታዊ መዋቅር



አባሪ 2

የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria)

የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues)	የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria)
1. ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውርን ሊያስከትሉ የሚችሉ ተግባራትን ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፤	1. የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል የፋይናንስ ተቋማት እና ለሎች የፋይናንስ ተቋም ያልሆኑ ተቋማት በየተቋማቸው ኮምፕሊያንስ ኦፍሰር /compliance officer/ እንዲያቋቁሙ እና ተግባራዊ እንዲያደርጉ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
	2. የፋይናንስ ተቋማት እና ሌሎች የፋይናንስ ተቋም ያልሆኑ ተቋማት የግብይት ሪፖርት በየወሩ ለማዕከሉ ማቅረብ ይገባቸዋል፡፡
	3. የፋይናንስ ተቋማት እና የፋይናንስ ተቋም ያልሆኑ ድርጅቶች ተጠርጣሪ ግብይቶችን ለማዕከሉ በየወሩ ሪፖርት ማድረግ ይገባቸዋል፡፡
	4. የፋይናንስ ተቋማት እና የፋይናንስ ተቋም ያልሆኑ ድርጅቶች የደንበኞቻቸውን ማንነት /customers identification and due diligence/ ጠንቅቀው ሊያውቁ ይጠበቅባቸዋል፡፡
	5. የፋይናንስ ተቋማት እና የፋይናንስ ተቋም ያልሆኑ ድርጅቶች ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመቆጣጠር የውስጥ ፖሊሲዎችና ቁጥጥር ሥርዓቶች እንዲኖራቸው እና ተግባራዊ እንዲያደረጉ ማዕከሉ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
	6. ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመከላከል ሀላፊነት የተሰጣቸው ሁሉም መ/ቤቶች ከተሰጣቸው ሀላፊነት እና ከ import & export ንግድ አንፃር ለህገ-ወጥ የገንዘብ ዝወወውር ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ የስጋት አካባቢዎችን ሊለዩ እና የተለየ ትኩረት በመስጠት እንዲቀሳቀሱ ማዕከሉ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
	7. በፋይናንስ ተቋማት ከውጭ ሀገር እቃ ለመግዛት ለውጭ ምንዛሬ የሚከፈተው ሌተር ኦፍ ኪሬዲት Letter Of Credit /LC/ እቃው ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ ለእቃው የተሰጠው የግዥ ደረሰኝ ከተሰጠው የውጭ ምንዛሬ ዋጋ ጋር እኩል መሆኑ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሊያረጋገጥ ይገባል፡፡
	8. የገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን እቃዎች በግዥ ከውጭ ሀገር በሚመጡበት ወቅት በዕቃው ደረሰኝ ዋጋ እና በሌተር ኦፍ ኪሬዲት የተሰጠው የውጭ ምንዛሬ ጋር ልዩነት ካለው ልዩነት መኖሩ እንደታወቀ ወዲያው ለማዕከሉ ሪፖርት የሚያደርግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
	9. ንግድ ሚኒስቴር እና ማዕድን ሚኒስቴር በህገ ወጥ ንግድ እና ህገ ወጥ የማዕድን ማውጣት ሥራ የሚጠረጥሩትን ማንኛውም ግለሰብም ሆነ ድርጅት ለማዕከሉ በየወሩ ሪፖርት የሚያቀርቡበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
	10. በሀገሪቱ ህገ-ወጥ የውጭ ምንዛሪ ግዥ እና ሽያጭ እንዳይኖር ብሔራዊ ባንክ የክትትል እና ቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
	11. የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ከማቅረብ ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን መነሻ፣ የአፈጻጸም ስልት፣ ዓይነት፣ ባህሪ እና አደጋ በማጥናት ዓመታዊ ሪፖርት ሊያዘጋጁና ለሚመለከታቸው አካላት ሊሰራጭ ይገባል፡፡
	12. የገቢ ወይም የወጪ ንግድ እቃዎችን ዋጋ ከተገዙበት ወይም ከተሸጡበት ትክክለኛ ዋጋ አስበልጦ ወይም አሳንሶ ማቅረብን (over or under invoicing of imported or exported goods) ለመከላከል ብሄራዊ ባንክ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ክትትል ሊያደርግ እና ለማዕከሉ በየወሩ ሪፖርት ሊያደርግ ይገባል፡፡
	13. የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን ብሔራዊ ባንክ የደነገጋቸው ሁኔታዎችና ግዴታዎች መሟላታቸውን ካላረጋገጠ በስተቀር ማናቸውም ዋጋ ያለው ዕቃ ወይም የውጭ ምንዛሬ ከኢትዮጵያ እንዳይወጡ ወይም እንዳይገቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡
	14. ማዕከሉ ማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል ስለተፈፀመው ህገወጥ ገንዘብ ዝውውርን ለመጠቆም ወይንም እንዲጠቁሙ ለማበረታታት አመቺ ግንኙነት መንገድ እና የህግ ከለላ የሚያገኙበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues)	የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria)
	15. ብሔራዊ ባንክ ህገወጥ የውጭ ሀገር ገንዘብ ግብይት ሊቆጣጠር እንዲሁም ግብይቱን ፈጽመው በተገኙት ግለሰቦች፣ ድርጅቶች፣ ጥምረቶች ወዘተ..... ላይም ህጋዊ እርምጃ ሊወስድ እና ለማዕከሉም በየወሩ ሪፖርት ሊያደርግ ይገባል፡፡
2. ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመከላከል የፋይናንስ መረጃ ሥርዓት ሊኖር እና ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፤	16. በውጭ ሀገራት የሚኖሩ እና በሀገር ውስጥ ያሉ አስቀጣሪ ኤጀንሲዎች የሰሩበትን ገንዘብ ወደ ሀገር ቤት ለመላክ የሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያ ኢንባሲም ሆነ በሌላ መንገድ ገንዘባቸውን የሚልኩበት ህጋዊ አሰራር ሊዘረጋ ይገባል፡፡
	17. ማዕከሉ ህገ-ወጥ ገንዘብ ዝውውር አስመልክቶ በሀገሪቱ ላይ ሊያስከትል የሚችለው አደጋ ጉልህነት ህብረተሰቡ እንዲገነዘብ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ በስፋት እና በተጠናከረ መልኩ ሊሰራ ይገባል፡፡
	18. ህገወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር እንዲያስችል በህግ ሀላፊነት የተሰጣቸው የመንግስትም ሆነ የግል ድርጅቶች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ሊያሰባስቡ፣ ሊያደራጁ፣ ሊያስቀምጡ እና በህግ ካልተከለከለ በስተቀር ለተቆጣጣሪ አካላት በተጠየቁ ጊዜ መረጃዎቹን ሊያቀርቡ ይገባል፡፡
	19. የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል በአዋጁ መሰረት የተቀበላቸውን ሪፖርቶች፣ ለህግ አስፈፃሚ አካላት የተመሩ ጉዳዮችን፣ ከተመሩት ውስጥ ምርመራ የተካሄደባቸውንና ክስ የተመሰረተባቸው የወንጀል ጉዳዮችን እና አለምአቀፍ ድጋፍ የተጠየቀባቸው ጉዳዮችን ጨምሮ ሥራውን በተመለከተ የተሟላ ስታትስቲክስ ሊይዝ ይገባል፡፡
3. ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመከላከል የተቀላጠፈ የባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ አሰራር ሥርዓት ሊኖር እና ተግባራዊ ደረጉን ማረጋገጥ፤	20. የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ከማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዝበ ከመርዳት ስጋቶች ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በአዋጁ መሰረት ሊሰበስብ፣ ሊያከማች፣ ሊፈትሽ፣ ሊተነትን እና ለሚመለከታቸው አካላት ሊያሰራጭ ይገባል፡፡
	21. የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል በህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውር ዙሪያ የመቆጣጠር እና የማስፈፀም ስልጣን ከተሰጣቸው የመንግስት መ/ቤቶች ጋር (ብሄራዊ ባንክ፣ ንግድ ሚኒስቴር፣ እንዱስትሪ ሚ/ር፣ የገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን ፣ ፌደራል ፖሊስ እንዲሁም ፀረ ሙስና ኮሚሽን ጋር በጋራ ለመስራት የመግባቢያ ሰነድ ሊኖረው ይገባል፡፡
	22. የጋራ መግባቢያ ሰነዱን የፈረሙ ዋና ባለድርሻ አካላት በሰነዱ መሰረት ህገወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመካለከል በጋራ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡
	23. ማዕከል እና ዋና ባለድርሻ አካላት ህገወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመከታተል እና ለመቆጣጠር ባለው ስርዓት ዙሪያ እንዲሁም የሚታዩ ክፍተቶችን እና የሚያጋጥሙ ችግሮች ዙሪያ ለመወያየት እና የጋራ የመፍትሄ ሀሳብ ለማግኘት ቢያንስ በሶስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ የመወያያ መድረክ ሊኖራቸው ይገባል፡፡
	24. ብሔራዊ ባንክ ማንኛውም ሀገር ውስጥ የሚገቡ እና የሚወጡ የውጭ ምንዛሬ ሊያስገኙ የሚችሉ ግብይቶችን በሚመለከት ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በጋራ በተቀናጀ ሥርዓት ሊዘረጉና ተግባራዊ ሊደርጉ ይገባል፡፡
	25. ብሔራዊ ባንክ ማንኛውም ሀገር ውስጥ የሚገቡ እና የሚወጡ የውጭ ምንዛሬ ሊያስገኙ የሚችሉ ግብይቶችን በሚመለከት ከገቢዎችና ግምሩክ ባለስልጣን በጋራ በተቀናጀ ሁኔታ ሊሰራ እና ተጠርጣሪ ግብይቶች ስያጋጥሙ ወዲያውኑ ለማዕከሉ ሪፖርት ሊያደርግ ይገባል፡፡
	26. ህገወጥ ገንዘብ ዝውውርን ለመከላከል ኃላፊነት የተጣለባቸው ባለድርሻ አካላት በጉዳዩ ዙሪያ የተወሰዱ እና የሚወሰዱ እርምጃዎችን የሚገልፅ እና በህገወጥ የገንዘብ ዝውውር ዙሪያ የተለዩ አዲስ ባህሪ ያላቸው ማናቸውንም ሁኔታዎች ያጠቃለለ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል በየሩብ ዓመቱ ሊቀርብ ይገባል፡፡

አባሪ 3

<u>በኦዲቱ ወቅት የታዩ ባለድርሻ አካላት ዝርዝር</u>

1. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
2. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
3. ንግድ ሚኒስቴር
4. ማዕድን ሚኒስቴር
5. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
6. የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን
7. የፌዴራል ስነምግባርና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን
8. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
9. የኢትዮጵያ ልማት ባንክ
10. ከግል ባንኮች
    - ✓ አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ
    - ✓ ዳሽን ባንክ
    - ✓ ዘመን ባንክ
    - ✓ አንበሳ ባንክ

ናቸው፡፡

የዋና ዋና ባለድርሻ አካላት የሥራ ግንኙነት

የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል

- ማዕከሉ በህገወጥ መንገድ የተገኘን ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን በተመለከተ ከሚመለከታቸው አካላት መረጃዎችን የመሰብሰብ፣ የመቀበል፣ የማከማቸት፣ የመመርመር፣ የመተንተንና የማሰራጨት ሥራ ይሰራል፡፡
- በተጨማሪም ወንጀሎችን በጥንቃቄ መርምሮ አግባብ ላለው የህግ አካል የማስተላለፍ፣ በአዋጁ መሰረት ኃላፊነት ያላቸው ሰዎች ተግባራቸውን ማከናወናቸውን ማረጋገጥ፣ የህዝቡን ንቃትና ግንዛቤ በማሳደግ የወንጀል ድርጊቱ ተጋላጭ እንዳይሆን ምቹ ሁኔታ መፍጠርን እና ከወንጀል ድርጊት ጋር በተያያዘ የመረጃ ልውውጥ ወይም የቴክኒክ ድጋፍ ከመንግስት አካላት ወይም ድርጅቶች እንዲሁም ከሌሎች ሀገሮች ተመሳሳይ ተቋማት ጋር የመግባቢያ ወይም ሌሎች ህጋዊ ስምምነቶች የመደራደርና የመፈራረም ሥራ ይሰራል፡፡

ብሔራዊ ባንክ

- ባንኩ ኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ፣ ነዋሪ ያልሆኑ እና ለጉብኝት የመጡ ሰዎች ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው የውጭ ምንዛሬ የሚይዝበትን ወይም በውጭ ምንዛሬ ክፍያ የሚፈፀምበትን ወይም የክፍያ ማዘዣዎችን የሚይዝበትን ሁኔታዎችንና ገደቦችን በተመለከተ እንዲሁም፤ ማንኛውም ወደ ኢትዮጵያ ወይም ከኢትዮጵያ ውጪ የሚተላለፍ የውጭ ምንዛሬ ፣ በወጪ ወይንም በገቢ ንግድ አማካኝነት ወደ ውጭ የሚላኩ ወይም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዋጋ ያላቸው እቃዎች በማናቸውም አኳኋን የኢትዮጵያን የጉምሩክ ድንበር አቋርጠው የሚወጡበት፣ እነዚህ እቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ የሚመለሱበት ፣ ወይም ከላይ የተገለፁት ወደ ውጭ የተላኩ ወይም ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ወይም ከውጭ የተመለሱ ዕቃዎች በውጭ ምንዛሬ ክፍያ የሚያስከትሉት ወይም ሊያስከትሉ የሚችሉትን ውጤት ለሚመለከቱ ግዴታዎችና ሁኔታዎች መመሪያ ያወጣል፡፡

የገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን

- ባለስልጣኑ ለገቢና ወጪ እቃዎች ቁጥጥርና ለታክስ አወሳሰን የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ በመስኩ ስለሚፈፀሙ ወንጀሎች የተሟላ የእስታቲክስ መረጃ ያጠናክራል፣ እንደ አስፈላጊነቱም ለሌሎች አካላት ያሰራጫል፤
- በጉምሩክ ወደቦች፣ በወሰን አካባቢዎች እንዲሁም በሌሎች የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎችና ማቋረጫ መስመሮች በኩል የሚገቡና የሚወጡ ዕቃዎችና ማጓጓዣዎችን

ይፈትሻል፣ የጉምሩክ ስነስርዓት ተፈፅሞባቸው መግባታቸውንና መውጣታቸውን ያረጋግጣል፤

- ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ወደ ሀገር የሚገቡትን ወይም ከሀገር የሚወጡትን ዕቃዎች እንቅስቃሴ የመቆጣጠር እና ኮንትሮባንድን የመከላከል ስራ በፌደራል ፖሊስ አማካኝነት እንዲካሄድ የመረጃ ልውውጥ ያደርጋል፣ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል ፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት ተገቢው እርምጃ እንዲወስድ ያደርጋል፤
- ብሄራዊ ባንክ የደነገጋቸው ሁኔታዎችና ግዴታዎች መሟላታቸውን ካላረጋገጠ በስተቀር ባለስልጣኑ ማናቸውም ዋጋ ያለው ዕቃ ወይም የውጭ ምንዛሬ ከኢትዮጵያ እንዳይወጣ ወይም እንዳይገባ ያደርጋል፡፡

ንግድ ሚኒስቴር

- ሚኒስቴሩ አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎቶችን ይሰጣል፣ የተሰጡ የንግድ ሥራ ፈቃዶች ለተሰጡበት ዓላማ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤
- የወጪና የገቢ ዕቃዎች በትክክለኛ ዋጋ ስለመሸጣቸው ወይም ስለመገዛታቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ክትትል ያደርጋል፤ ዋጋ አሳንሰው በሚልኩ ወይም በሚያስመጡ ላይ በህግ አግባብ እርምጃ ይወስዳል፤
- የሀገር ውስጥ ንግድ እንዲስፋፋና ህጋዊ የንግድ አሠራር እንዲሰፍን ተገቢነት ያላቸውን እርምጃዎች ይወስዳል፤

በገቢ እና ወጪ እቃዎች የነጋዴዎች ኃላፊነት

- ማንኛውም ነጋዴ የጉምሩክ ዲክራላሲዮን በሚጠይቅበት ጊዜ የማጓጓዣ ሰነድ፣ የዋጋ ሰነድ፣ የባንክ ፈቃድ ፣ የዕቃ ዝርዝር መግለጫ ሰነድ፣ የስሪት ሀገር መግለጫ የምስክር ወረቀት እና ለሚከተሉት ሰነዶችና ዋና ቅጂ የገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን በሚወሰነው ብዛት አዘጋጅቶ በአባሪነት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን

- ከፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል ከቀረበለት መረጃ፣ በራሱም ጥረት ያገኛቸውን እና ለሌሎች የመንግስት እና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት በሰበሰባቸው መረጃዎች መሰረት በህገወጥ የገንዘብ ዝውውር ላይ የሚሳተፉትን ድርጅቶች እና ግለሰቦች ለህግ ያቀርባል አስፈላጊው የህግ እርምጃ እንዲወሰድባቸው መረጃዎችን ለህግ አካላት ያቀርባል፡፡